አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ከዓለም ኤኮኖሚ ጋር የተቆራኘ ባለመሆኑ ዓለም አቀፉ ቀውስ አይነካንም፣ ኤኮኖሚያችንም 11 በመቶ ያድጋል ብሎ ከዋሸ ብዙ ጊዜ ሳያልፍ ዓለም አቀፍ እርዳታ በአፋጣኝ ካልተደረገልን መፈራረሳችንና ሕዝብም ለሞት መዳረጉ ነው ብሎ ልመና መግባት ተገዷል። የኤኮኖሚ እድገት ያለውም የሕልም እንጀራ እንደሚሆንና 5 በመቶም ዕድገት ከተገኘ ተዓምር መሆኑን አማካሪዎቹም አስጠንቅቀውታል። በመጋቢት መጨረ ሻ ላይ በለንደን ከተማ በእንግሊዝ ሀገር በሚደረገው የ 20 ሀብታም ሀገሮች የኤኮኖሚ ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ ሊለምን የታጨው መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ለረሀብ መጋለጡን ሊደብቅ አልቻለም።

የአገዛዙ መካከለኛ ስታቲስቲክስ ቢሮ ራሱ እንደገለጠው በኢትዮጵያ የምግበና የሌሎች ቆሳቁሶች ዋጋ ካለፈው ዓመት ሲነፃፀር በ65 በመቶ ጨምሯል። በትምባሆና አልኮል ብቻ ሳይሆን በህክምና አገልግሎት ላይም የመጣው የዋጋ ግሽበት ሕዝብን ለባሰ ችግር እየዳረገው መሆኑም ተገልጧል። ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ያለውን የኀይል ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ መብራት ሀይል በፈረቃ ሊሰራጭ መጀመሩን ማወቅ ተችሏል። ይህ ምንም እንኳን የተከዜ ግድብ በቂ ውሀ ባያገኝም በትግራይ ከተሞች አልተከሰተም የተባለው የኤሌክትሪክ ሀይል ዕጥረት በምር ት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግርን እየፈጠረ መቀጠሉ ተነግሯል። የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት መለስና ቤተሰቡና ወያኔዎቹ በጭካኔ እየዘረፉ ባለበት ሁኔታ ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተብዬው ደግሞ የባለስልጣናትን ንብረት መመዝገብ የሚያዝ ህግ ረቂቅ ማሰናዳቱን ለማወቅ ተችሏል። ይህ ህግ ረቂቅ በግልፅ ጠቅላይ ሚኒስቴሩንና ፕሬዚዳንቱን የሚመለከት አይደለምም ተብሏል። ሌሎች ባለስልጣኖች፣ሚኒስቴሮች፣ምክትሎች፣ ፓርላማ ተመራጮች ዳኞች አምባሳደሮች ወዘተ የገቢያ ቸውን ምንጭና ልክ ማሳወቅ አለባቸው የሚለው የህግ ረቂቅ የፓርላማ አባል የሆነችውን የመለስ ን ሚስት አዜብ ጎላንም ይመለከታታል ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው ተብሏል።በሙስና የተዘፈቀት ጀኔራሎችና የወያኔ ቁንጮዎች እነ በረከት ስምዖን፣ ስብሐት ነጋ፣ ስዩም መስፍን፣ አባዱላ ገመዳ፣ አዲሱ ለገሰ ወዘተ ም የሀብታቸውን ልክ የሚያሳውቁ አይሆኑም ሲል ሕዝብ ይተቻል። ስለዚህም የዚህ ንብረታችሁን አሳውቁ ህግ ዋና ዓላማ ዝቅተኛና ወገን አልባ ተሿሚዎችን ንብረት ለማወቅ ና ለመንጠቅ ነው የሚል ድምጻሜ ከወዲሁ አለ ።

በየካ እና በአራዳ ክፍለ ከተሞች አዋሳኝ ላይ የሚገኘውና ከ60 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረውና ቀበና ድልድይ መፍረሱ አግባብ እንዳልሆነና የአገርን ቅርስ ማሳጣት መሆኑን ብዙ ዜናች ገልጠዋል። በትግራይ ምድር በሀውዜን፣ ሽሬ እንዳ ስላሴ ወዘተ ቱሪስት አልባ ቦታዎች ዘመናው ሆቴሎችን ገንብቶ ሚሞካሻው ወያኔ በሌሎችና ቦታዎች ያሉ ቅርሶችን በዕብሪት ማፍረሱ አነጋጋሪ ሆኖ ቀጥሏል።

በቅርስነት ተመዝግቦ ለትውልድ ሲተላለፍ መኖር እንደነበረበትና ለአገሪቷም የእድገትና ሥልጣኔ አመጣጥን እንደ አንድ ምስክር ወይም ማስረጃነት ይቆጠር እንደነበር የሚነገርለትን ድልድይ እንዲፈርስ ያደረገው የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን መሆኑን ነዋሪዎቹ ይናገራሉ።

የቀበና ድልድይ በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት በሩስያ ተወላጆች የተሰራ ታሪካዊ ድልድይ ነበር።የሚፈርሱ ቤቶች እንዲጠበቁ፣ ፎቶ እንዲነሱ፣ በፊልም እንዲቀረፁና ቅርስነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ኮሚቴ

ተቋቁሞ እንደነበርና መንቀሳቀስ ከጀመረ በኋላ ምክንያቱ ሳይታወቅ እንቅስቃሴ ማቆሙን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያን ንብረት በተለይም በቤተክርስቲያኖች ያሉ ታሪካው ቅርሶችን በምስጢር እያወጡ መሸጡ አሁንም የቀጠለ ሲሆን የቆዩ የብራና ጻዊቶችና መፅሀፍት በእንግሊዝ፣ፈረንሳይና አሜሪካ ም ውስጥ ለውስጥ እየተሸጡ ነው ተብሏል፡፡ በዚሁ ንግድ ደግሞ የወያኔው ጳጳስና ባለስልጣናት እንደሉበት ታውቋል፡፡ ከዚህ በተያያዘም ህፃናትን ለባዕድ መሸጡ አትራፊ ንግድ ሆኖ በመገኘቱ ባለፈው ዓመት ከኢትዮጵያ የተሸጡ ህፃናት ቁጥር ከሀይቲና ሌሎች ሀገሮች መብለጡንም ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ከ 5 ሚሊዮን ያላነሱ ዕጓለ ምውታን ልጆች ያሉ ቢሆንም ለጉዲ ፈቻ የሚሸጡት ቤተሰብ ያላቸውም ጭምር ናቸው ተብሏል፡፡ ወንድምና እህት ተነጣጥለው ለልዩ ልዩ ፈረንጆች መሸጣቸውም የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

መለስ ዜናዊ መጪውን ምርጫ 99 በመቶ ድምፅ አግኝቶ ለማሸነፍ በሚያደርገው ሩጫ የኢሕአ ዴግ አባላት ቁጥር ወደ 5 ሚሊዮን መድረሱ ሲታወቅ አምባገነኑ ደግሞ የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች በካድሬዎቹ ሞልቶ ማነጋገሩን ቀጥሎበታል፡፡ በቀን መቶ ብር አበል የተሰጣቸው 7ሺ ተማሪዎችን ካነጋገረ በኋላ ባለፈው ሰሞን ደግሞ እንዲሁ አበል የተሰጣቸውን አስተማሪዎችን ሰብስቦ አነጋግሯል፡፡ በዚሁ ስብሰባ የወያኔ ካድሬ አስተማሪዎች ሲለፍፉ ሌሎች በዝምታ ማቆየታ ቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ግን ወደ 50 የሚጠጉ ዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች ለ 6 ወር ደሞዛቸው እንዳልተከፈላቸው አማረው ተቃዋሞ አሰምተዋል፡፡ በእንድርያስ እሸቴ አማካኝነ ት ፍርስርሱ የወጣው ዩኒቨርስቲ ተቋም በባዕድ አስተማሪዎችና በተለይም ምንም ችሎታ በሌላቸ ው ግን ከአገዛዙ ጋር በታማኝነት በመተሳሰራቸው ወይም ዲፕሎማ ባይኖራቸውም ከክልል አንድ በመወለዳቸው ብቻ የዩኒቨርስቲ አስተማሪ በተባሉ የተሞላ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ድንጋይ ማምረቻ ከሚባለውም የወያኔ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ተመርቀው ሲያበቁ የዩኒቨርስቲ አስተማሪ የተባሉም አሉ፡፡ የወያኔ አገዛዝ የአስተማሪዎችን ማህበር አፍርሶና መሪዎቹን አሳዶና ገድሎ ግፍ መፈፀሙ የሚታወስ ነው፡፡ በመጪው ምርጫ የመለስ አገዛዝ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ከወዲሁ የደመደመ እንደመሆኑ መጠን በዚሁ ቧልት ለመሳትፍ የተዘጋጁትን ተቃዋሚዎች ሕዝቡ እየታዘ ባቸው መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተያያዘ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ክፍል ሀላፊ ( ብዙዉን ጊዜ የአሜሪካ የስለሰላ ድርጅት ሲአይ ኤ ሽፋን ነው ይህ ቦታ) የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪዎች እየነጋገረ መሆኑ ተዘግቧል፡፡ የዚህ ንግግር ዋና ዓላማ በ1997 ቪኪ ሀደልስተን የተቃዋ ውሞ አድማን አክሽፋ ለወያኔ እንደጠቀምችው ሁሉ ተቃዋሚ ሀይሎችን ለወያኔ የምርጫ ጋሪ ተጎታች ለማድረግ ነው ተብሎ ተተችቷል፡፡ የወያኔ አገዛዝ የምርጫ ህጉና ኮሚሽኑን ሳይቀይርና የታሰሩትንም ሁሉ ሳይፈታ፣ አፈናውን ሳያቆምና ምርጫን ዳግም ለማጭበርብር መጣሩን ሳያቆ ም በምርጫ ለመሳተፍ መዘጋጀት ዳግም ራስንም ሕዝብንም ለወያኔ ሰለባ ማድረግ ነው ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ያሳስባሉ፡፡

በመላ ሀገሪቷ እያየለ የመጣው የኤኮኖሚ ቀውስ፣ የውጭ ምንዛሪ መጥፋት፣ ረሀብ መስፋፋት፣ የመብራት ሀይል መጥፋት፣ የኑሮ ውድነት ወዘተ  የአገዛዙ የከሰረ የፖለቲካና የኤኮኖሚ መስመ ር ውድቀት መሆኑን ለመሸፈን መለስ ዜናዊ የባጡን የቆጡን ቢቀባጥርም አገዛዙ ክስረት እንዳጋ ጠመው መደበቅ አልቻለም:: ወደ ሶማሊያ ጦር ልኮ የህይወትም የገንዘብም ኪሳራ በሀገር ላይ ማምጣቱም ተጋልጧል:: በሰሞኑ በኦብነግ ና ኦነግ ሀይሎች ላይ ድልን ተቀዳጀሁ በሚል የኦብነ ጉን መሪ ዶክተር መሀመድ ሴሪን አስከሬንና የተማረከውን የኦነግ አመራር አባል ፉርጋሳን በቴሌ ቪዥን ቢያሳይም በኦጋዴን ገፅ አሳሳቢ ሁኔታ መፈጠሩን መደበቅ አልተቻለውም:: ተያይዞም በገ ሬዎችና በቦረና ተወላጆች መሀል የተፈጠረወ. ግጭትና የወያኔ ካድሬዎች ይህን ግጭት ሲያራግ ቡ ዓመታት ማሳለፋቸው፣ ወደ ኬንያ ናይሮቢ ዘልቀው የቦረናውን መሪ ጃተኔ አሊን ከዚህ ቀደም መግደላቸው ወዘተ ሁሉ ዛሬ እየተባባሰ ያለ የጦርነትና የቀውስን ሁኔታ ማሳየቱ ግልፅ ሆኗል:: የወያኔ ካድሬዎችና የሶማሊያ አማፅያን በቦረና ያሉትን ሶማሌዎች (ገሬዎች) አስታጥቀውና ደግፈው በኦሮሞዎች ላይ ማነሳሳታቸውና ቀደም በግጦሽ የነበሩ መለስምቅሮ ግጭቶች ከዚህ አስከፊ ደረጃ መድረሳቸው ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ በየቦታው እያጠመደው ያለውን የክፍፍል ፈንጂ ያጋልጣል ሲሉም ጉዳዩን የተከታታሉ ጠቁመዋል:: በኤኮኖሚወ መስክ በዚህ ዓመት ለገበ ያ የቀረበው ቡና መጠኑ ማነሱና አምራቾች የወያኔ አገዛዝ አቀቀቀምኩት በሚለው የኤሌክትሮኒ ክ የምርት ልውውጥ ተቋም ላይ እምነት ማጣታቸውን ለመደበቅ በዘመነ ደርግ ይሰማ የነበረውን የአሻጥረኛ ነጋዴ ቀረርቶ መለስ ዜናዊም ደግሞት የቡና አምራቾችን በመወንጀል እጃችሁን እቆርጣለሁ፣ የደበቃችሁትን ቡና እወርሳለሁ ብሎ ሲደነፋና ራሱንም ለትዝብት ሲያጋልጥ በሰሞ ኑ ተደምጧል::

ወደ ዓለም የንግድ ድርጅት ለማገባትም ያቀረበውን የአባልነት ጥያቄ በተመለከተ ምዕራባውያን በባንኮች መስክ ለውጥ እንዲደረግና ቴሌኮሙኒኬሽንም ለግል ባለሀብቶች እንዲሸጥ ወይም መስኩ ክፍት እንዲሆን ጠይቀዋል:: የወያኔ የሞኖፖል ቁጥጥርና የኢንተርኔትና የቴሌፎን አገል ግሎት ውድቅ ደረጃ ላይ መሆኑም ተጠቅሷል::የወያኔ አገዛዝ ቴሌፎኖችን ይጠልፋል፡ ድረ ገፆችን ያግዳል፣ ለአገልግሎት የሚያስከፍለውም ዋጋ ከብዙዎች አቅም በላይ መሆኑ ተጋልጧል:: በኬንያ ለምሳሌ የእጅ ቴሌፎን ሲም ካርድ በ 5 ዶላር ሲሸጥ በኢትዮጵያ ዋጋው 35 ዶላር ነው ሲሉ ምዕራባውያኑ ተችተዋል:: ከወያኔ አገዛዝ በኩል በግርማ ብሩ አማካይነት የተሰጠው መልስ ግን በቴሌኮሙኒኬሽንም ሆነ ባንኩ መስክ ምንም ለውጥ እንዳማይደረግ ነው:: የወያኔ አገዛዝ ከቻይና ባልተናነሰ የራሱን ብቸኛ ቁጥጥር በቴሌኮሙኒኬሽን፣ኢንተርኔትና ሌሎች መገናኛ ብዙሃ ን ላይ በማድረግ የሕዝብን መብት ያግዳል በሚልም ተወግዟል::

ከሀዲው አገዛዝ የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን አስረክቦ ብሄራዊ ወንጀልን ከፈፀመ ጊዜ ጀምሮ የሕዝብን ተቃውሞ ከመጤፍ ሳይቆጥር በክህደቱ ጎዳና እንደቀጠለ የታወቀ ነው:: በቅርቡ የሱዳንና የወያኔ ባልስልጣኖች ተገናኝተው በጋራ ተቃዋሚዎችንና ስደተኞችን ለማፈንና

ለማስጨነቅና በተለይም ጋምቤላን በተመለከት የመሬት ጉዳይም ላይ ውይይትና ስምምነት አድር ገዋል:: በሱዳን ነዋሪ የሆነ የኢትዮጵያ ስደተኞች ብዙ ስቃይ እያዩ ሲሆን ወያኔ በሱዳን እንደልቡ እንዲንቀሳቀስ ተፈቅዶለት ስደተኞችን እንደሚያጠቃና ወደ ኢትዮጵያም በግድ ተይዘው እንዲ መለሱ እንደሚያደርግ ታውቋል:: ተይዘው ከተመለሱት ውስጥ ደብዛቸው የጠፋ ብዙዎች ሲሆኑ ባለፈው ተጠልፈው ከመጡት 15 ኡ ውስጥ አዛውንቱ ሻለቃ አጣናው ዋሴ ጤንነታቸው መተጓጓ ሉም ታውቋል:: የሱዳን ጦር በነፍሶ ገበያ ተራራ ገፅ በቋራ ኢትዮጵያ መሬት ላይ ሰፍሮ እስካሁን መገኘቱንም ከአካባቢው የደረሰን ዜና ያረጋግጣል:: ወደ ጋምቤላ ደግሞ ቤንዚን ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተውን መሬት ለሱዳን ለማስረከብ ወያኔ ተስማምቷል መባሉም መታወስ ያለበት ነው:: ለማንኛውም የሱዳኑ የፀጥታ ተቋም ሃላፊ ሳላህ አብደላ ጎሽ የሱዳንና የወያኔ ስብሰባ የተሳካ መሆኑን ገልፆ ግንኙነታችንን ሊያበላሹ የሚያሴሩትን እንዋጋቸዋለን ሲል ዝቷል::

የአሜሪካ የተሳሳተ ፖለቲካ የሚቀጥል ከሆነ በአፍሪቃ ቀንድ ላለው ቀውስ መባባስ ዋና ምክንያት ሊሆን መቻሉ ተጠቆመ :: በአዲስ አበባ የአሜሪካ አምባሳደር የነበረው ዴቪድ ሺን ለአሜሪካ ኮን ግሬስ በሰጠው መግለጫ የወያኔን አገዛዝ የተቸ መስሎ በመደገፍና በ1997 ኡን እልቂት ሳይቀር በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ ለማለከክ በመሞከር የአሜሪካ አስተዳደር አፍቅሮ አሜሪካ ያለ ውን የወያኔው አገዛዝ ምንም እንኳን የሕዝብን ሰብዓዊ መብት ከመጠበቅ አንፃር ግልፅ ድክመት ቢኖረውም በአካባቢው የአሜሪካንን ፖለቲካና ፍላጎት አስፈፃሚ በመሆኑ ይህንን በግንዛቤ በማስገ ባት በሚገባ መያዝ ያስፈልጋል ሲል መክሯል:: በመሰረቱ ወያኔ ሕዝብን ቢበድልም ቢፈጅም ሎሌያችን ስለሆነ እንቀፈው ሲል ፖለቲካን አዋቂ ተብዬው ዴቪድ ሺን መክሯል:: የአፍሪቃ ቀንድ ሀገሮች ቀውስ የተያያዘ ከመሆኑ በላይ አሜሪካ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም አስቀድማ ከአምባገነኖች ጋር መያያዟ ለቀውሱ መወሳሰብና መባባስ ዋና ምክንያት ሆኖ ሳለ ይህን በመካድ አሁንም ቢሆን ለአሜሪካ እስካደሩ ድረስ መለስንም የጅቡቲውንም ኦማር ገሌ አቅፈን ደግፈን እንቀጥል የሚለው ፖለቲካ ተደጋፊ ከሆነ የአፍሪካ ቀንድ ቀውስ በአሜሪካ እየተባበሰ መሄዱ የሚጠበቅ ነው ተብሏል:: የመለስ አገዛዝ በቅርቡ ከቻይናና ሩስያ ጋር ይበልጥ የተቀራረበ ግንኙነ ት ለመመስረት መጣሩም የሚታወቅ ነው:: አሜሪካና እንግሊዝ አሁንም ለወያኔ አገዛዝ ድጋፍ እየሰጡ መሆናቸውን ሕዝብ መዘንጋት የለበትም ተብሏል::

የወያኔ መገናኛ ብዙሃን እንዳቀረቡት ከሆነ በአዲስ አበባ ያሉት የእስራኤል አምባሳደር ቤን ሀይ ም ኤርትራ ለፍልስጤሙ ሀማስና ለአፈሪቃ ቀንድ ሽብርተኞች የመሳሪያና የወታደራዊ ስልጠና እርዳታ እየሰጡች ናት ብለው ከሰዋል ተብሏል:: አምባሳደሩ አውነትም ይህን ይበሉ አይበሉ ባይ ረጋገጥም ወያኔ አገዛዝ ከጅቡቲ ጋር በመቀራረብ የጅቡቲና የኤርትራን ግጭት ሊያባብስና ሊጠ ቀምበት መጣሩ ሲታወቅ ኤርትራም በበኩሏ ፀረ ወያኔ ሽምቅ ተዋጊዎችን እየረዳች መሆኑ ምስ ጢር አይደለም:: ይህ በዚህ እንዳለ ግን በትግራይ መሬት ያለው የኤርትራ ስደተኞች ሰፈር ውስ ጥ ያሉት ሺዎች ኤርትራውያን ሳይሆኑ ከኤርትራ በጦርነቱ ጊዜ የተባረሩ የትግራይ ተወላጆች ናቸው ሲል አንድ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅት መሪ ነኝ የሚል ግለሰብ ከሷል::